ጤናሚኒስቴር - ኢትዮጵያ
Ministry of Health - Ethiopia
የዜጎችጤናለሀገርብልጽግና!
Healthier Citizens for Prosperous Nation

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የጤና ሚኒስቴር

# የውጪ ሀገር የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት ማስተግበሪያ መመሪያ

ጥር 2017 ዓ/ም

## በኢትዮጲያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት የጤና ሚኒስቴር
## መመሪያ ቁጥር…/2017

## የውጪ ሀገር የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት ማስተግበሪያ መመሪያ

ለሕክምና ወደ ውጪ ሀገር የሚሄድ ኢትዮጵያዊ ጤንነቱ፤ደህንነቱ እና ክብሩ ተጠብቆ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ የሚያስችል የሕግ ማእቀፍ ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

በሀገር አቀፍ ደረጃ የውጪ ሀገር የሕክምና ቅብብሎሽን ወጥ የሆነ አተገባበር ስርዓት በመዘርጋት አላስፈላጊ የታካሚን እንግልት መቀነስ፣ ለህክምናው አስፈላጊ የሆኑ ነገሮችን በተሟላ መልኩ የተቀላጠፈ አገልግሎት ለመስጠት አስፈላጊ ሆኖ በመገኘቱ፤

የጤና ሚኒስቴር የጤና አገልግሎት፣አስተዳደር እና ቁጥጥር አዋጅ ቁጥር 1362/2017 አንቀጽ አንቀፅ 58(2) መሰረት ይህን መመሪያ አውጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ
## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### 1.አጭር ርዕስ

ይህ መመሪያ "**የውጪ ሀገር የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት ማስተግበሪያ መመሪያ** ቁጥር…/ 2017” ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### 2. ትርጓሜ

የቃሉ ወይም የሀረጉ አገባብ የተለየ ትርጉም የሚያሰጠው ካልሆነ በስተቀር በዚህ መመሪያ ውስጥ፡-

1) **“ሆስፒታል“** ማለት በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ወይም ከዛ በላይ ደረጃ የተሰጠው ሆስፒታል ወይም ኮምፕርሄንሲቭ ሆስፒታል በሌለባቸው ክልሎች፤ በቢሮው የተመረጠ አጠቃላይ ሆስፒታል ነው::

2) **“ታካሚ”** ማለት የህክምና አገልግሎት ለማግኘት ወደ ውጭ ሀገር የሚሄድ ግለሰብ ነው፡፡

3) **“ታካሚውን የተከታተለው ሀኪም”** ማለት ታካሚው ከሚታከመው የህመም ዓይነት ጋር በቀጥታ የሚገናኝ ትምህርት የተማረ ስፔሻሊስት ወይም ሰብስፔሻሊስት ነው፡፡

4) **“የውጪ ሀገር የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ”** ማለት ታካሚ የሕክምና አገልግሎት እንዲያገኝ ሚኒስቴሩ ከሀገር ውስጥ የጤና ተቋም ወደ ውጪ ሀገር የሚገኝ የጤና ተቋም የሚያሸጋግርበት ስርዓት ነው፡፡

5) **“ቦርድ”** ማለት በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር የተቋቋመ አደረጃጀት ነው፡፡

6) **“የቦርድ ማስረጃ”** ማለት ታካሚው ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ መታከም እንዳለበት የሚገልጽ በቦርድ የተሰጠ የሕክምና ማስረጃ ነው፡፡

7) **“ቢሮ”** ማለት የውጭ ሀገር ህክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ ሥርዓት መተግበርን የሚያረጋግጥ የክልል ጤና ቢሮ ወይም የአዲስ አበባ የምግብና መድሀኒት ቁጥጥር ባለስልጣን ነው፡፡

8) **“ሚኒስቴር” ወይም ”ሚኒስትር”** ማለት እንደ ቅደም ተከተሉ የጤና ሚኒስቴር ወይም ሚኒስትር ነው፡፡

9) **“ክልል”** ማለት በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ-መንግስት አንቀጽ 47 መሰረት የተቋቋመ ክልል ሲሆን የአዲስ አበባ እና ድሬደዋ ከተማ አስተዳደሮችን ይጨምራል፡፡

10) **“ሰው”** ማለት ማንኛውም የተፈጥሮ ሰው ወይም በሕግ የሰውነት መብት የተሰጠው አካል ነው፡፡

11) ማንኛውም በወንድ ፆታ የተገለፀ አገላለፅ የሴት ፆታን ይጨምራል፡፡

**3.<u>የተፈፃሚነት ወሰን</u>**

ይህ መመሪያ፡-

1) ወደ ውጪ ሃገር ለህክምና በሚሄድ ታካሚና አስታማሚ፣

2) በሆስፒታል፣

3) በውጭ ሀገር ሕክምና ለሚሰጥ ጤና ተቋም በሀገር ውስጥ በሚገኘው ህጋዊ ወኪል፣

4) በሚኒስቴሩ፣እና

5) በቢሮ፤ላይ

ተፈፃሚ ይሆናል፡፡

## ክፍል ሁለት

## የውጪ ሀገር የሕክምና አሰጣጥ ቅብብሎሽ

### 4.ለውጪ ሀገር ህክምና የሚያበቁ ሁኔታዎች

ታካሚው በሚኒስቴሩ በኩል ወደ ውጭ ሀገር ሕክምና ማግኘት የሚችለው፦

1) ሕክምናው በሀገር ውስጥ ሊሰጥ የማይችል ከሆነ (የህክምና መመርመሪያ መሳሪያው ከሌለ፣ የህክምና አገልግሎቱን መስጠት የሚችል ባለሙያ ከሌለ) ወይም ለምርመራ የናሙና ዝውውር የማይቻል መሆኑ በሚመለከተው አካል ሲረጋገጥ፤

2) የዚህ አንቀፅ ንኡስ(1) ድንጋጌ ቢኖርም የሕክምና አገልግሎቱን በሀገር ውስጥ ለማግኘት በረጅም ወረፋ ምክንያት ጊዜ የሚወስድ ከሆነና ታካሚው አገልግሎቱን ሳይወስድ መቆየቱ በጤናው ላይ የማይመለስ ጉዳት እንደሚደርስ በቦርድ ከተረጋገጠ ወደ ውጪ አገር ሄዶ እንዲታከም ሚኒስቴሩ ሲፈቅድ፤ወይም

3) በውጭ ሀገር ለተሰጠ የህክምና አገልግሎት ታካሚው የህክምና የክትትል ቀጠሮ እንዳለው ከታከመበት የጤና ተቋም ማስረጃ ካቀረበ እና በቦርድ ለክትትል መሄዱ ሲወሰን ነው፡፡

### 5.የውጭ ሀገር ህክምና አገልግሎት ለማግኘት መሟላት ስለሚገባቸው ማስረጃዎች

1) ታካሚው ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ ህክምና ለማግኘት የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማሟላት አለበት፦

ሀ. ማንነቱን የሚገልጽ የታደሰ መታወቂያ (የነዋሪነት ወይም የብሄራዊ ወይም ዲጂታል መታወቂያ) ወይም የኢትዮጵያ ፓስፖርት ወይም የልደት ምስክር ወረቀት)

ለ. ስድስት ወር ያላለፈው ሶስት ጉርድ ፎቶ ግራፍ፤

ሐ. ሶስት ወር ያላለፈው የተሟላ የቦርድ ማስረጃ፤

2) የዚህ አንቀፅ ንኡስ አንቀፅ(1) ድንጋጌ እንደተጠበቀ ሆኖ ለንቅለ ተከላ ህክምና የሚከተሉትን ማስረጃዎች ማሟላት አለበት፦

ሀ. ከውልና ማስረጃ የተቀባይ እና ለጋሽ እንዲሁም የለጋሽ ቤተሰብ የተዋዋሉበትን የሰነድ ማስረጃ፤

ለ. የለጋሽ የጤና ምርመራ ማስረጃ፤

## 6.ስለውጭ ሀገር ታካሚ አስታማሚ

1) ቦርዱ አሳማኝ ሆኖ ሲያገኘው በውጭ ሀገር እንዲታከም ከተፈቀደለት ታካሚ ጋር የሚሄድ እስከ ሁለት አስታማሚ ሊፈቀድ ይችላል፡፡

2) እድሜው ከ 18 ዓመት በታች ለሆነ ታካሚ ወላጅ ወይም በሕግ ሞግዚትነት የተሰጠው ግለሰብ አስታማሚ ሆኖ አብሮ መሄድ አለበት፡፡

3) ከታካሚው ጋር አብሮ እንዲሄድ የተፈቀደለት አስታማሚ፤ ከታካሚው ጋር አብሮ መሄድ አለመቻሉን የሚያስረዳ አሳማኝ የሆነ ማስረጃ ከሚመለከተው ህጋዊ ተቋም ከቀረበ ሚኒስቴሩ አስታማሚው እንዲቀየር ሊፈቅድ ይችላል፡፡

# ክፍል ሶስት
# ስለ ቦርድ

## 7.የቦርድ አመሰራረት

1) ቦርዱ በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ይቋቋማል፡፡

2) ቦርዱ የሙያ ስብጥርን፤የስራ ልምድን፣ የሙያ ስነ- ምግባርን እና የስፔሻሊቲ ወይም የሰብስፔሻሊቲ ደረጃ መስፈርቶችን መሰረት ባደረገ መልኩ ይሆናል፡፡

3) የቦርዱ የአባለት ቁጥር ከ3 ያላነሰ ከ5ያልበለጠ መሆን አለበት፡፡

4) የቦርዱ ሰብሳቢ በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ይመረጣል፡፡

5) ሆስፒታሉ የቦርዱ የአሰራር ስርዓት፣የቦርድ አባላት የስራ ዘመን፤ እና ሌሎች ዝርዝር ጉዳዮች ይህንን መመሪያ መሰረት አደርጎ ግልፅ በሆነ መንገድ የመተዳደርያ ደንብ ያዘጋጃል፡፡

## 8.ስለ ቦርድ ተግባርና ኃላፊነት

ቦርዱ የውጭ ሀገር ሕክምና ቅብብሎሽ በተመለከተ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) የውጭ ሀገር ህክምና ውሳኔ ለመስጠት በሳምንት አንድ ጊዜ ይሰበሰባል፤ሆኖም አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በማንኛውም ጊዜ ይሰበሰባል፡፡

2) ከቦርዱ አባላት ከግማሽ በላይ የሚሆኑት በስብሰባው ላይ ከተገኙ ምልዓተ ጉባዔ ይሆናል፡፡

3) ታካሚውን ከተከታተለው ሀኪም የታካሚው የሕክምና ማስረጃ በደረሰው በ10 የሥራ ቀናት ውስጥ ውሳኔ መስጠት አለበት፤

4) ቦርዱ የወሰነውን ውሳኔ ለሜዲካል ዳይሬክተሩ በ03 የሥራ ቀን ውስጥ ለማጸደቅ መላክ

አለበት፡፡

5) ለሜዲካል ዳይሬክተሩ የተላከው ማስረጃ ከ3ባላነሰ የቦርድ አባላት የተፈረመ መሆን አለበት፡፡

## 9.ታካሚውን የተከታተለው ሀኪም ተግባር እና ሀላፊነት

ታካሚውን የተከታተለው ሀኪም፡

1) ህክምናው በሀገር ውስጥ ሊሰጥ እንደማይችል እና ህመሙ መታከም የሚችል መሆኑን ማረጋገጥ አለበት፡፡

2) ወደ ውጭ ሀገር ሄዶ የህክምና አገልግሎት እንዲያገኝ የተፈለገበት አግባብ እና የሕክምናው ውጤት ማስረጃ ለታካሚው ማሳወቅ አለበት፡፡

3) ታካሚው ለውጭ ሀገር ህክምና መስማማቱን የሚገልጽ የስምምነት ቅጽ ማስሞላት እና ማስፈረም አለበት፡፡

4) የተሟላው መረጃ በ3 የስራቀናት ውስጥ ለቦርድ መስጠት አለበት፡፡

## ክፍል አራት

## የሚኒስቴሩ፣የቢሮ እና የሆስፒታል ተግባርና ኃላፊነት

### 10. የሚኒስቴሩ ተግባርና ኃላፊነቶች

ሚኒስቴሩ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) ከሆስፒታሉ የተላከው የቦርድ ማስረጃ ያረጋግጣል፣ያጸድቃል

2) አገልግሎቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

3) የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ያጠናክራል፣ ያዘምናል፤

4) የአሰራር መመሪያዎች ያዘጋጃል፤ተፈጻሚነቱን ይከታተላል፤ ይገመግማል፤

5) ከባለድርሻ አካላቶች ጋር የቅንጅታዊ አሰራር ስርዓት ይዘረጋል፤

6) ለውጪ ሀገር ታካሚ የቦርድ ማስረጃ ቅጽ እና ሌሎች ቅጾችን ያዘጋጃል፤ ለሚመለከታቸው ሆስፒታሎች ያሰራጫል፣

7) የቦርድ ማስረጃውን መሰረት በማድረግ ወደ የሚመለከተው የመንግስት ተቋም የድጋፍ ደብዳቤ ይጽፋል፤

8) በዚህ መመሪያ አንቀጽ (15) መሰረት በውጭ ሀገር ህክምና የሚሰጠውን የጤና ተቋም እንዳስፈላጊነቱ ያለበትን ሁኔታ በአካል በመገኘት ያረጋግጣል፤

9) በሀገር ውስጥ የማይሰጡ የሕክምና አገልግሎቶችን ይለያል፤ ለሚመለከታቸው አካላት ያሳውቃል፤

10) በማንኛውም ጊዜ በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (9) የተመለከተውን አገልግሎት በሚያዘጋጀው የብሄራዊ የሕክምና አገልግሎት መዘርዝር መረጃ ቋት ሊተካ ይችላል፡፡

## 11. የቢሮው ተግባርና ኃላፊነት

ቢሮው የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) በሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ፀድቆ የተላከውን የቦርድ ማስረጃ ያረጋግጣል፣ያጸድቃል፡፡

2) የጸደቀውን የቦርድ ማስረጃ ወደ ሚኒስቴሩ ይልካል፤

3) አገልግሎቱን ዲጂታላይዝ ለማድረግ አስፈላጊውን ድጋፍ ያደርጋል፤

4) የመረጃ አያያዝ ስርዓትን ያጠናክራል፣ ያዘምናል፡፡

## 12. የቦርድ ማስረጃ የሚያጸድቀው ኃላፊ ተግባርና ኃላፊነት

1. ቦርድ ያቀረበለትን የሕክምና ማስረጃ መመሪያው ባስቀመጠው መሰረት የተሟላ መሆኑን ያረጋግጣልያጸድቃል፤

2. የፀደቀውን የቦርድ ማስረጃ ለሚኒስቴሩ ይልካል፡፡

## 13. የቦርድ ማስረጃ ስለሚያረጋግጥ ባለሙያ ተግባርና ኃላፊነት

የቦርድ ማስረጃ የሚያረጋግጥ ባለሙያ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) የተላከው አገልግሎቱን መስጠት ከሚችል ሆስፒታል መሆኑን ያረጋግጣል፤

2) ማስረጃው የተሟሉ መሆናቸውን ያረጋግጣል፤

3) በተዘጋጀው ቅፅ መሰረት በሚመለከተው ባለሙያ የተሞላ እና ስምና ፊርማዎቹ ትክክለኛ መሆናቸውን ያረጋግጣል፡፡

## 14. የውጪ ሀገር ታካሚ ቅብብሎሽ ማስረጃ ስለሚሰጥ የሆስፒታል ተግባርና ኃላፊነት

ሆስፒታሉ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

1) የውጪ ሀገር ታካሚ ቅብብሎሽ ማስረጃ መስጠት የሚችለው በህግ ስልጣን በተሰጠው አካል የኮምፕሬንሲቭ ስፔሻላይዝድ ወይም ከዛ በላይ ደረጃ የተሰጠው ሆስፒታል ወይም ኮምፕርሄንሲቭ ሆስፒታል በሌለባቸው ክልሎች ፤በቢሮው የተመረጠ አጠቃላይ ሆስፒታል ነው፡፡

2) በስራ ላይ ያሉ የቦርድ አባላት ስምና የፊርማ ናሙና ወዲያውኑ ለሚኒስቴሩ ወይም ለቢሮው ማሳወቅ አለበት፡፡

3) የቦርድ ማስረጃው በተቋሙ ቦርድ የተረጋገጠ መሆኑን ማጣራት አለበት፡፡

4) ሜዲካል ዳይሬክተሩ የቦርዱ ሰነድ የተሟላ መሆኑን ለሚኒስቴሩ ወይም ለቢሮው በ3 የሥራ ቀን ውስጥ አጽድቆ መላክ አለበት፡፡

5) የተቀየሩ የቦርድ አባላት ስም ዝርዝር ለሚኒስቴሩ ወዲያውኑ ማሳወቅ አለበት፡፡

6) በሚኒስቴሩ የተዘረጉ የአሰራር ስርዓቶችን መከተል እና መተግበር አለበት፡፡

15.<u>ለውጭ ሀገር ታካሚ በውጭ ሀገር የህክምና አገልግሎት ስለሚሰጥ የጤና ተቋም እና ወኪል</u>

1) የጤና ተቋሙ የሥራ ፈቃድ ያለው ስለመሆኑ የሚያሳይ ማስረጃ ሆስፒታሉ የሚገኝበት ሀገር ባለው በኢትዮጵያ ኤምባሲ በኩል የተረጋገጠ ማስረጃ ስለመኖሩ ለሚኒስቴሩ ማቅረብ አለበት::

2) ለታካሚው በውጭ ሀገር የህክምና አገልግሎት የሚሰጥ የጤና ተቋም በሀገር ውስጥ የተመዘገበ ህጋዊ ወኪል ያለዉ እና በሚኒስቴሩ ይሁንታ ያገኘ መሆን አለበት፡፡

3) የጤና ተቋሙ ወኪል ስለ ጤና ተቋሙ የሚጠየቀውን ማስረጃ ማቅረብ የሚችል መሆን አለበት፡፡

4) የጤና ተቋሙ ወኪል ጤና ተቋሙ ለሚሰጠዉ የህክምና አገልግሎት ጥራት ደረጃ ጉድለት ፤የህክምና ስህተት ወይም የሙያ ግድፈት ካሳ መክፈል አለበት፡፡

## <u>ክፍል አምስት</u>

## <u>የቅሬታ አቀራረብና አፈታት ሥርዓት</u>

16. <u>*የቅሬታ አቀራርብ ሥርዓት*</u>

1) በዚህ መመሪያ አንቀጽ 9(4) መሰረት በተቀመጠው የጊዜ ገደብ ውስጥ ታካሚውን የተከታተለ ው ሀኪም የተሟላ መረጃ ለቦርድ ካላቀረበ ታካሚው ካወቀበት ጊዜ ጀምሮ ቅሬታውን ለሜዲካል ዳይሬክተሩ በ5የስራቀናትውስጥ ማቅረብ ይችላል፡፡

2) ቦርዱ የውጭ ሀገር ህክምና በተመለከተ በታካሚው ሀኪም የቀረበለትን የሕክምና ማስረጃ ከተቀበለ በኋላ በዚህ መመሪያ አንቀጽ (8) መሰረተ በተመለከተው ጊዜ ውስጥ ካልወሰነ ታካሚው በ1 ወር ጊዜ ውስጥ ቅሬታውን ለሜዲካል ዳይሬክተሩ ማቅረብ ይችላል፡፡

3) ቦርድ በሰጠው ውሳኔ ላይ ማንኛውም ቅሬታ ያለው ታካሚ ቅሬታውን የቦርድ ውሳኔ በደረሰው በአስር የሥራ ቀን ውስጥ ለሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ማቅረብ ይችላል፡፡

4) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ(1)፣(2) እና (3) መሰረት ቅሬታ የቀረበለት የሆስፒታሉ ሜዲካል ዳይሬክተር ቅሬታው በቀረበለት በ5 የሥራ ቀን ውስጥ ምላሽ መስጠት አለበት።

5) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (4) መሰረት ቅሬታ ሰሚው አካል በሰጠው ውሳኔ ላይ ቅሬታ ያለው ታካሚ ውሳኔው በደረሰው በ5 የሥራ ቀናት ውስጥ ለሆስፒታሉ ሥራ አስኪያጅ ማቅረብ ይችላል።

6) ታካሚው በሚኒስቴር መስሪያ ቤቱ ጉዳዩ የሚመለከተው የሥራ ክፍል በውጭ ሀገር ሕክምና ለማግኘት በሚቀርብ ጥያቄ ላይ በሚሰጠው ማንኛውም ውሳኔ ላይ፤ውሳኔው በተሰጠ በ10 የሥራ ቀን ውስጥ ለሥራ ክፍሉ ኃላፊ ቅሬታውን ማቅረብ ይችላል።

7) በዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ (6)ላይ በተሰጠው ውሳኔ ቅሬታ ካለው ውሳኔ በተሰጠበ5 የሥራ ቀን ውስጥ ለሚኒስትሩ ማቅረብ ይችላል።

## ክፍል ስድስት

## ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች

### 17. የመተባበር ግዴታ

1) ይህ መመሪያ ተፈጻሚ ይሆንባቸዋል ተብለዉ በመመሪያው የተጠቀሱ አካላት በሙሉ ለመመሪያዉ ተፈጻሚነት የመተባበር ግዴታ አለባቸው።

2) የዚህ መመሪያ ድንጋጌ ሲጥስ የተገኘ ማንኛውም ሰው አግባብ ባለው ሕግ መሰረት ተጠያቂ ይሆናል።

### 18. ተፈፃሚነት የማይኖራቸው መመሪያዎችና አሰራሮች

ከዚህ መመሪያ ጋር የሚቃረን ማንኛውም መመሪያ ወይም ልማዳዊ አሰራር በዚህ መመሪያ ውስጥ በተሸፈኑ ጉዳዮች ላይ ተፈፃሚነት አይኖረውም።

### 19. መመሪያዉ ተፈፃሚ የሚሆንበት ቀን

ይህ መመሪያ በሚኒስትሩ ተፈርሞ በፍትሕ ሚኒስቴር ከተመዘገበ እና በድሕረ ገፅ ላይ ከተጫነበት ጊዜ ጀምሮ ተፈፃሚ ይሆናል።

**መቅደስ ዳባ (ዶ/ር)**

**የጤና ሚኒስቴር ሚኒስትር**

**አዲስ አበባ፣ኢትዮጵያ**